# ፕላስቲኮች እንደ አልማዝ ዘላለም ኗሪ ናቸው







ፕላስቲኮችን ለኛ ጠቃሚ እንዲኾኑ የሚያደርጓቸው ጥንካሬያቸው እና ለማመን የሚያስቸግር ረዥም ዕድሜያቸው ሲኾኑ ፣ እነዚህ ጠቃሚ ባሕሪዎቻችው የዱር አራዊት ቀንደኛ ገዳይም ያደርጓቸዋል ፣ በተለይም በባሕራዊ ከባቢ ውስጥ ወድቀው ሲገኙ።
የባሕር ውስጥ እንስሳት በፕላስቲኮች ይተበተባሉ ፤ በዋጧቸውም ጊዜ ወይ ታንቀው ፣ አሊያም በውስጥ አካሎቻቸው ላይ በሚደርስ ጉዳት የተነሣ ይሞታሉ።
የተፈጥሮ አካባቢ በጣም በፍጥነት መራቈት አንዳንዴ ተስፋ አስቈራጭ መኾኑ ለኹላችንም ይገባናል። የማይገታ ከሚመስል ኺደቱ አንጻር ልናደርግ የምንችለው በጣም ትንሽ መኾኑ እንዲሰማን ያደርገናል። በፕላስቲኮች የሚመጣ የአካባቢ ብክለትን በተመለከተ ግን ልናደርግ የምንችለው በርግጥ አለ።በተለይ “ሲክስ ፓክ ሪንግስ” የሚባሉት የፕላስቲክ ማሰሪያ ቀለበቶች ሕይወት አጥፊ ናቸው።
የአዕዋፍን ፣ የዓሦችን እና የጋፎችን ዐንገት በማነቅ ፣ የዶልፎኖችን ሙርሙርት እና የሲሎችን መቅዘፊያ ቅሳሮች በማፈን ይከረክራሉ ፤ ክፉኛም ያቈስሏቸዋል። ቊስሎቹ ለልክፈት (ኢንፌክሽን) ሲጋለጡ ደግሞ ፣ ክፉኛ ለሚያሰቃይ እና በቀስታ ለሚገድል ሞት ይዳረጋሉ።
ባለስድስት እሽግ ሽቀጥ በገዙ ቍጥር ፣ ወይም ባለስድስት ማሸጊያ መንገድ ላይ ወድቆ ቢያገኙ ፕላስቲክ ቀለበቶቹን ይበጥሱ ፤ መንገድ ላይም ወይም ባሐር ውስጥ ከመጣል ይቈጠቡ ፤ ፕላስቲክ ሪሳይክል በሚደረግበት ማጠራቀሚያ ውስጥ ይክተቱት። ይህን ቀላል ተግባር በመፈጸም ምንም እንስሳ በነርሱ ተጥምዶ እንዳይሞት ትብብር ያደርጋሉ። እንዲህ ለማድረግ የሚወስድብዎት ጥቂት ስከንዶች ብቻ ነው ፤ የድርጊትዎ በጎ ውጤት ግን ዘላቂ ሊኾን ይችላል።የፕላስቲክ ብክለትን በተመለከተ ፣ ምን ለማድረግ እንደሚችሉም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ድር-ገጽ ይጎብኙ ፡
http://www.apusenvironment.com/plasticpollution